# ወይ ፣ሱሪህን ፍታ

የአማራው ጀግንነት ፣ ቀድሞ የሰማሁት
እውነትማ ቢሆን ፣ ዛሬም ላይ ፣ ባየሁት
ታሪክም ፣ ተረት ነው ፣ ዘመን ከተሸኘ
ትውልዱም አክብሮት ፣ ይዞት ካልተገኘ
ዛሬ የምናየው ፣ አሳዳጅ ተሳዶ
ሃቅን ካልተጋታት ፣ ሳይወዳት ተገዶ
ያማራው ጀግንነት ፣ ይባዛል በባዶ
መሞቱ ሳይበቃ ፣ እንደ ሙክት ታርዶ
ዘላለም ይኖራል ፣ ተረግጦ ተዋርዶ ።

አንድ ፣ ለሺ ነበርክ ፣ የቋራው አንበሳ
ምድር አንቀጥቅጡ ፣ የጎንደሩ ካሳ
አንተን ፣ ማን ይተካህ ፣ ጦርህን ፣ ማን ያንሳ
አገርም የለህም ፣ ታሪክህ ተረሳ
ይኸው ታነባለች ፣ አገር ተቆራርሳ
ቁጭት ይቀስቅስህ ፣ እባክህ ተነሳ ።

የተከልከው ችግኝ ፣ መቼም አላሸተ
ባቀናኸው አገር ፣ እየተዘበተ
በልጅ ፣ ልጆችህ ላይ ፣ እየተዘመተ
ባራቱም ማዕዘን ፣ አማራ እየሞተ
አሻፈረኝ ብሎ ፣ ህዝቡም አልሸፈተ
ትንሹም ትልቁም ፣ ባማራው ተበተ
እሬሳ መቁጠሩ ፣ ለቁጥር ታከተ ።

የጊዜ አጋጣሚ ፣ ካለበት ቢያደርሰው
ሚስትህን ሲደፍራት ፣ ጎጆህን ሲያፈርሰው
እንደንሰሳ ሲያርዱህ ፣ ተፈጥረህ እንደሰው
ያባትህን ጓንዴ ፣ ከምንትተራሰው
ጋሻና ጦርህን ፣ ትኋን ከሚወርሰው
ማገዶ ታድርገው ፣ ሚስትህ ትቆስቁሰው
አንተም ፣ ማጀት ገብተህ ፣ ቀሚሷን ልበሰው ።

በታጋሽነት ስም ፣ በወሬ ቱማታ
በጠባቦች መድረክ ፣ በጠባብ ገበታ
በአራዊት ፣ ፍርድ ቤት ፣ ተሟግተህ ላትረታ
ህዝብ ከማስፈጀት ፣ ወገን ከሚመታ
እስኪ ለወገንህ ፣ ዋልለት ውለታ
እንደወንዶች መክት ፣ ሁን ላገር ፣ መከታ
ወይ ፣ ዝናርክን ታጠቅ ፣ ወይ ፣ ሱሪህን ፍታ ።

ታዛቢው

May 1, 2019